# የስደተኞች መጠለያ የቤት ስነስርዓት

የስደተኛ መጠለያ ውስጥ እንደሚኖር ሰው የቤት ስነስርዓት ማክበር ይጠበቅብዎታል። ስነስርዓቱ የተወሰነው እርስዎና ሌሎች ነዋሪዎች አስተማማኝና ጥሩ የመኖሪያ ሁኔታ እንዲኖራችሁ ነው።

## 1 ጸጥታ፣ ስርዓትና ደህንነት

- በስደተኞች መጠለያ ከ 23 ሰዓት እስከ 6 ሰዓት ድረስ ጸጥታ መሆን አለበት።
- መረበሽም ሆነ ለሌሎች ደስ የማይል ስሜት የሚሰጥ ባህርይ ማሳየት የለብዎትም። ጥቃት፣ ነገሮችን ማበላሸትና ሌሎች ህገ ወጥ ድርጊቶች ለስደተኞች ቢሮ (ለዩዲአይ)ና ለፖሊስ ሪፖርት ይደረጋል።
- በጋራ መጠቀሚያ አካባቢዎች ላይ አልኮል መጠጣት የለብዎትም።
- ሲጋራ፣የዉሃ ፒፓና የኤሌክትሪክ ሲጋራን በጋራ መጠቀሚያ ወይም በክፍልዎ ማጨስ የለብዎትም።
- በስደተኛ መጠለያ የቤት እንስሳት አይፈቀድም።
- አንድ ድንገተኛ ሁኔታ ቢፈጠር ወይም በስደተኛ መጠለያ እሳት ቢነሳ ምን ማድረግ እንዳለብዎ መማር አለብዎት።

## 2 የክፍልና የእቃ አጠቃቀም

- የጋራ ክፍልና የውጪ አከባቢ በጽዳት መያዝ አለብዎት። ብስክሌቶች፣ የህጻናት መግፍያና ሌሎች እቃዎች በአደጋ ጊዜ ማምለጫ መንገድ እንዳይዘጉ ጥንቃቄ ማድረግ አለብዎት።
- ክፍልዎን በጽዳትና ስርዓት መያዝ አለብዎት።
- ቆሻሻን እንደየ ዓይነቱ መለያየትና በቆሻሻ መጣያ መጣል ይኖርብዎታል።
- የጋራ መጠቀሚያ ክፍሎችን ውስጥ በየጊዜው ማጽዳት አለባችሁ። የርስዎ የማጽዳት ተራ መቼ እንደሆነ የሚያሳይ ዝርዝር ተዘጋጅቷል። የርስዎ ተራ ሲደርስ ማጽዳት አለብዎት።
- የልብስ ማጠቢያ፣ የኩሽና እቃዎችንና የማጽጃ እቃዎችን አጠቃቀሙን በመከተል መጠቀም አለብዎት።

## 3 የአዳር ጎብኚ ስያገኙ

- ለአዳር እርስዎ ጋር የሚመጣ ጎብኚ ሲኖው አስቀድመው ከስደተኛ መጠለያ ኃላፊዎችን ማሳወቅ ያስፈልግዎታል።
- የስደተኛ መጠለያ ኃላፊዎች አዳር ጠያቂን መከልከል ይችላሉ።
- ሁሉም እርስዎ ጋር የምያድሩት በኖርዌይ የሚኖሩና ህጋዊ መታወቂያ ወይም የስደተኞች መታወቂያ ለስደተኛ መጠለያው ሰራተኞች ማሳየት አለባቸው።
- የአዳር ጠያቂ ሲኖርዎት ሌሎች የስደተኛ መጠለያ ነዋሪዎችን እንዳትረብሹ ጥንቃቄ ማደረግ አለባችሁ።
- ለጠያቂዎችዎ ምግብና የመኝታ ልብስ ማዘጋጀት የርስዎ ኃላፊነት ነው።
- አንድን አዋቂ ሰው በሌላ የስደተኞች መጠለያ የሚኖሩ የራሱ ልጆች፣ ጓደኞችና የቤተሰብ አባል ለአዳር መጎብኘት ይችላሉ።
- አንድ ከ18 ዓመት በታች የሆነ ልጅም ወላጆቹ፣ ወንድሞቹና የእድሜ እኩያ ጓዳኞቹ በአዳር ሊጎበኙት ይችላል።

## 4 ለቆ መውጣት

- ቤቱን ለቀው ሲወጡ ክፍልዎ ወይም ቤትዎ የተስተካከለና በደንብ የጸዳ መሆን ይኖርበታል።
- ከስደተኛ መጠላያ ለቀው ሲወጡ የቤቱን ቁልፍ ማስረከብ ይኖርብዎታል።

ቀን

ፊርማ